International Ethiopian Woman Organization IEWO
ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት (ዓኢሴድ)

IEWO, 1515 South 4th street #1801, Minneapolis, MN 55454, USA

መስከረም ፲፱. ፪ ሺ. ፪

# ሕጻናትን ሸቀጥ ማድረግ ይቁም!!

**ዓለም ዓቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት (ዓኢሴድ) በጉዲፈቻ ስም የኢትዮጵያን ሕጻናት ማጋዝ እንዲቆም ማድረግ የማንኛውም ስብአዊ ፍጡር ሁሉ ግዴታ ነው ብሎ ያምናል።**

በቅርቡ የአውስትራልያ የዜና ማሰራጪ ቴሌቪዥን ABC ለእይታ ያቀረበውና በተለያዩ የኢትዮጵያውያን ድረ ገፆች ላይ የቀረበው ዘገባ በማደጎ ስም በሃገራችን ሕፃናትና እናቶች ላይ እየተፈጸመ ያለውን ኢሰብዓዊና ግብረገብነት የጎደለው ተግባር አጋልጧል።

ሕጻናት በተለያዩ ሰውሰራሽም ሆነ ተፈጥሯዊ ችግሮች ወላጅ አልባ በሚሆኑበት ጊዜም ሆነ፣ ወላጆች ልጆቻቸውን በድህነት ወይም በበሽታ ምክንያት መንከባከብ አቅቷቸው፣ ሕፃናት የመንገድ ላይ ተዳዳሪዎች እንዳይሆኑ ለማድረግ  የአንድ ሃገር መንግሥትም ሆነ የበጎ አድራጎት ስጪዎች የመጀመሪያዉ ተግባር መሆን ያለበት ሕጻናቱ በዚያው በተወለዱበት ሃገር ምግብ፣ መጠለያና ሌሎች ለመኖር አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁስት እንዲሟሉላቸው፣ የትምህርት ብሎም የስራ እድል የሚያገኙበትን ሁኔታዎች በማመቻቸት ወደ ስራ ዓለም እንዲሄዱና አምራች ዜጎች እንዲሆኑ ማድረግ ሲሆን ሌላው ተግባር መሆን ያለበት ለወላጆች የስራ እድልን በመፍጠር የወለድዋቸውን ልጆች የማሳደግ አቅም እንዲኖራቸው ማድረግ ነው።

www.aesed.org

aesed.iewo@gmail.com

ሃገራችን ኢትዮጵያ ይህንና ይህን የመሳሰሉ ተግባራትን በማከናወን ጤናማ ዜጎች ተወልደው የሚያድጉባትና ሀገራቸውን ከድህነት፣ ከኋላቀርነት አላቀው የሚኖሩባት ሃገር እንድትሆን የሕዝብን ሰብዓዊ ተፈጥሯዊና ዲሞክራሲያዊ መብት የሚያከብር፣ የሃገሪቱን ሃብት ለሃገር እድገት፣ ለዜጎቿ የትምህርትና የስራ እድል መፍጠሪያ፣ ጤናቸውን መንከባከቢያ የሚያደርግ ስርአት መፍጠር ዋነኛውና አማራጭ የሌለው ዘላቂ መፍትሄ ነው ብሎ ዓለም ዓቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት (ዓኢሴድ) ያምናል። ስለሆነም ዛሬ በሃገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ የሕዝብና ለሕዝብ የቆመ መንግሥት ባለመኖሩ የሕብረተሰባችንን ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች መፍትሄ አልባ እያደረገው ይገኛል ።

የኢትዮጵያ ፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢ..ፖ.እ.አ.ኮ) ረዘም ላሉ ዓመታት ሲያስታውቅ እንደኖረው ወላጅ አልባ ብቻ ሳይሆን ወላጅ ያላቸው ሕጻናትም በገፍ በማደጎነት ወደ ውጭ ሃገር እየተላኩ እንደሆነና እናቶች ልጆቻቸውን ለማሳደግ በማይችሉበት ደረጃ ላይ ሲደርሱ በተስፋ መቁረጥ ሁኔታ ውስጥ እየገቡና እንዲሁም በሚነገራቸው የተሳሳቱ ማግባቢያዎች ለባዕዳን አሳዳጊዎች ልጆቻቸውን ለመስጠት ተገደዋል ።

ምንም እንኳን ዓለማችን ዛሬ በሚልዮን የሚቆጠሩ ሕጻናት በጦርነት፣ በበሽታና በረሃብ ወላጅ አልባ የሆኑባት ብትሆንምና ኢትዮጵያም በዚሁ ከፍተኛ ችግር ካለባቸው ሃገሮች ውስጥ በ ፳ ተኛ ተራ ብትመደብም ሕጻናትን እንደ ንግድ ዕቃና የምርት ሸቀጥ በዓመት አንድ መቶ ሚልዮን የአሜሪካ ዶላር የውጭ ምንዛሪ

International Ethiopian Woman Organization IEWO
ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት (ዓኢሴድ)

IEWO, 1515 South 4th street #1801, Minneapolis, MN 55454, USA

ማስገኛ አድርጎ ለመጠቀም የሚያስችል መንገድ መከፈቱ በእጅጉ መኮነን ያለበት ድርጊት ነው።

ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ከ ፳ በላይ የሚሆኑ ሕጻናትን በማደጎ ወደ ባዕዳን አገሮች በገፍ የማጋዝ ተግባር ላይ የተሰማሩ የበጎ አድራጎትና

የሃይማኖት ድርጅቶች ነን ባዮች ከ ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ መንግሥት ጋር በመሆን የኢትዮጵያን ሕጻናት ከወላጆቻቸው እየነጠሉ ከትውልድ ሃገራቸው በማውጣት መነገዱን በከፍተኛ ደረጃ ተያይዘውታል።

ዓለም ዓቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት (ዓኢሴድ) የተባበሩት መንግሥታት አባል አገሮች ሁሉ የፈረሙበት ዓለም ዓቀፍ የሰብአዊ መብት ማስጠበቂያ ድንጋጌዎች እንዲሁም ባለ ፲ አንቀጹ የሕጻናትን መብት ማስከበሪያ ሕጎች በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲከበሩ የሚመለከታቸው ሁሉ የበኩላቸውን እንዲያደርጉ እየጠየቀ በማደጎ ስም በኢትዮጵያ ሕጻናትና እናቶች ላይ የሚደረገው የግፍ ንግድ ባስቸኳይ እንዲቆም ያሳስባል ።

በኢትዮጵያ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ይከበሩ!!

በሕጻናት መነገድ ባስቸኳይ ይቁም!!

ዓለም ዓቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት (ዓኢሴድ)

www.aesed.org

aesed.iewo@gmail.com